# መምርያ ለበጎ ስራ መስራት የሚፈልጉ ጥገ ነት ፈላጊዎችና ስደተኞች

(ይህን ዝርዝራዊ ፅሁፍ ከ "Use Your Skills" ("ችሎታህን ተጠቀምበት") ከሚለው ጠቅላላው በራሪ ፅሁፍ አብሮ መነበብ አለበት)

**እንግሊዝ አገር ውስጥ የበጎ ስራ መስራት በፍላጎትህ ስለሆነ የሚያስገድድህ የለም፣ በውድህ ትሰራለህ።**

## <u>የበጎ ስራን መምረጥ (Choosing the volunteering activity)</u>

እንግሊዝ አገር ውስጥ የተለያዩ የበጎ ስራ አይነቶች ይገ ሉ። ለእርዎ የሚመች ግን እንደት ይመርጣሉ? ግምት ውስጥ ማስገባት የሚገባዎትን ጉዳዮች አሉ፤:

- የበጎ ስራ ለመስራት ሲፈልጉ ኢንፎርመሽን የት ያገ ሉ? ለጓደኞች ወይም ማህበሩን በቀጥታ ማነጋገር ይችላሉ። ምንም አይነት ኢንፎርመሽን ከሌልዎት ወይም ምክር ከፈለጉ፣ የበለጠው አማራጭ ወደ Volunteer Centre (የበጎ ሰራተኞች ማእከል) መሄድ ነው። ይህ ምህበር ደግሞ በአከባቢው የሚገ - የበጎ ስራዎችና በሚፈልጉት ስራ እንዲሰማሩ እርዳታ ያቀርባል።

- ምን ያህል ትርፍ ግዜ አልዎት? በሳምንቱ ነፃ የሚሆኑበትን ቀን መቼ ነው? አብዛኞቹ የበጎ ስራዎች በሳምንት ቢያንስ እስከ አንድ ሰዓት እንዲሰሩ የሚይስፈቅዱ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ እንደ የምክር ማእከል የበጎ ስራ፣ ስልጠና ጨምረህ በሳምንት ከሁለት እስከ ሶስት ቀን እንዲሰሩ የሚያስችሉ ናቸው። የሚከፈለው የምክር ሰራተኛ ለመሆን ቢያንስ ዓመት ወይም ከዛ በላይ የበጎ ስራ መስራት ይኖርብሃል።

- ያሉህን ግዚያቶች ምን ያህል አመቺ ናቸው? አንዳንዱ የበጎ ስራዎች ናፃ በሃኦንክበትና በተመቸህ ግዜ መጥተህ እንድትሰራ የሚያስችሉ ሲሆኑ አንዳንዱ ግን የሚሰጡት አገልግሎቶች በበደጎ አድራጊዎች ስለሚሰሩ፣ አስቀሞ በተያዘ ቀጠሮ ወይም በተወሰነ ግዜ መጥተው እንዲሰሩ የሚፈልጉ ናቸው። ለምሳሌ፣ የምክር አገልግሎት ሰጪዎች ለሶስት ወር ያህል ሁሌ ሰኞ ከጥዋቱ 10:00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4:00 ሰዓት እና ለስልጠና ደግሞ ሁሌ ሓሙስ ከጥዋቱ 9:30 ሰዓት እስከ ምሽቱ 3:00 ሰዓት እንዲመጡ ይጠይቃሉ።

- ምን አይነት ስራ ላይ መሰማረት ይፈልጋሉ? ምክር? አትክልተኛነት? አዛውንቶችን መርዳት? የህፅ -ሳናቶችን ስራ? እንግዳ ተቀባይ? አስተናጋጅነት? የኮምፕዩተር ስራዎች? ሰፊ አማራጮች ስላሉ መጠየቅ ይገባል

- ችሎታዎ ምንድን ነው? ሌላ ቋንቋ መናገር ይችላሉ ወይ? ከሌሎች የምግባባት ችሎታ አልዎት ወይ? ተፈጥሮአዊ ችሎታ አልዎት ወይ? የማስተማር ልምድ አልዎት ወይ? የገንዘባዊ ሂሳብ ችሎታ አልዎት ወይ? የሆነ ችሎታ አልዎት ወይ? ይህን ያልዎትን ችሎታ በመጠቀም የሚሰሩበትን ስራ ሊያገ - ይችልሉ።

- የእንግሊዘኛ ችሎታዎ ምን ያህል ነው? አንዳንዱ የበጎ ስራዎች ብዙ እንግሊዘኛ መቻል አያስፈልጋቸውም። ለምሳሌ እንደ አትክልተኛነት፣ የሙያ ስራዎች ወይም ቡና ማቅረብ። ሌሎች እንደ ምክር ወይም እንግዳ ተቀባይ ግን ከፍተኛ የእንግሊዘኛ ችሎታ ይጠይቃሉ። ለማንኛውም ሊሰሩት የሚችሉ ነገር ስለማይታጣ መጠየቅ ነው።

- **የወንጀል መዝገብ ጽህፈት ቤት ማረጋገጫ (Criminal Record Bureau (CRB) Disclosure)** አንዳንዱ የበጎ ስራ ዕድሎች የ CRB ወይም Police "Disclosure/Check" (የፖሊስ ማረጋገጫ) የሚባለውን የመልከቻ ፎርም እንድትሞላ ይጠይቃሉ። ይህም የበጎ ስራ የሚሰራውን ከዚህ በፊት የወንጀል መዝገብ ካለው ለማረጋገጥ ነው። ይህን የሚያስጨንቅ ጉዳይ አይደለም፣ እና በጥገ ነት ጥያቄዎ የሚያመጣው ለውጥ የለም። ምህበሩ ስለ ህፃናቶችና በቀላሉ ተጠቂ የሆኑ ሰዎች ሃላፊነት ስለሚወስድ። ከህፃናቶችና በቀላሉ ተጠቂ ከሆኑ ሰዎች ጋር የበጎ ስራ የሚሰራ ሰው ይህን ማረጋገጫ ወረቀት ማምጣት አለበት። ለበጎ ስራ ለሚሰሩ ሰዎች፣ ልጥገ ነት ፈላጊዎችና ስደተኞች ይህን በናፃ ይሰጣል። ማህበሩ ደግሞ ይህን ፎርም ለመሙለት ይተባበራቹሃል።

## ቀጠሮ መያዝ፣ ስብሰባዎችና የበጎ ስራ ግዚያቶች
**(Arranging appointments, meetings and volunteering times)**

- **ጊዝያቶችን ማስተካከል፣ ማንኛውም ሰው ቀጠሮ መያዝ ወይም የበጎ ስራ መስራት ከፈለገ፣ የምይመች ከሆነ ወድያውኑ መንገር ይገባል። ማስታወስ ያለብዎት ወድያውኑ "አይቻልም" ማለቱ ሊመጡ ከሚችሉ አለመግባባቶች ያስወግዳል። ከቤተሰብዎ፣ ኮሌጅ ወይም ሌላ ጉዳይ ካለብዎት ለሌላ ቀን እንዲተላልፍ ሃሳብ ማቅረብ ይችላሉ።**

- **ሰዓትን ማክበር፣ የበጎ አድራጊ ሰራተኛ በመሆንህ መጠን ሰዓትን መለየትና ማክበር ይገባሃል። ስራውን ለመስራት ወይም ለስልጠና የማይመችህ ከሆነ፣ ማህበሩን ሌላ አማራጭ ለመፈልግ ስልክ ደውለህ መንገር ይገባል።**

- **የማህበሮች የምልመላና የአመራረጥ ደንቦች ሊቀያየር ይችላል። ይህ የሚያካትተው እንደ፣ የመመልከቻ ፎርም፣ ቃለ መጠይቆች፣ ተጠያቂዎች፣ የ** CRB **ማረጋገጫዎችና የመፈተኛ ወቅት የመሳሰሉ ናቸው። ለማመልከቻ ሂደት እርዳታ ከፈለጉ የ** Volunteer Centre **ሊረዳዎት ይችላልል። የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታዎ ዝቅተኛ ከሆነ፣ ማመልከቻውን ለመሙላት ማህበሩ ሊተባበራቹ ይችላል። ለአንዳንድ የበጎ ስራዎች ለመስራት ከስራው በፊት ወይም በኋላ ስልጠና እንዲካፈሉ ይጠይቃል።**

- **ወጪዎች፣ አንዳንድ ማህበሮች አስቀድሞ በተያዝው ቀጠሮ መሰረት፣ ለስብሰባ ሲመጡ ነጉዞ ለሚያወጥዋቸው ወጪዎች ይከፍላሉ። ይህ ግን የብጎ ስራዎን ሳይጀምሮ ላለው ግዜ ነው።**

## የበጎ ስራዎን ሲጀምሩ (Once you have started volunteering)

- **ቃል መግባትና ታማኝነት፣ ቃልን በማክበርና ታማኝነትን በማሳየት ጥሩ ሪፈረንስ ለምግኘት ትችላለህ። ብዙውን ግዜ ስራ ሰጪዎች ስራ ሲሰጡ የሚያይዋቸውን ነገሮች ቢኖሩ ቃልን ማክበርና ታማኝነት ነው።**

- **ተቆጣጣሪ፣ ተቆጣጣሪ እንዲኖርህ ይገባል። ከማህብሩ እንድትወሃሃድ፣ ጥቄ ወይም ችግር ካለብህ ሊረዱህ፣ ስልጠና ላይ ሊያስመዘግቡህና ድጋፍ ሊሰጡህ ይችላሉ። ሪፈረንስ ስለሚጽፉልህ ከተቆጣጣሪህ ሁልግዜ መመካከር ጥሩ ነው።**

- **ቀጠሮን ማክበር፣ ለቀጠሮህ በግዜህ መገ ት አለብህ። ያማይመችህ ከሆነ ለምሳሌ ከታመምክ፣ ደውለህ መንገር አለብህ።**

- **ወጪዎች፣ ለምታወጣቸው ወጪዎች እንደ የጉዞ፣ ምሳ፣ የአፀደ ህፃናት የመሳሰሉት እንድትከፈል መብት አለህ። የወጪዎች መጠየቂያ ፎርም እና እንዴት እንደሚሞላ ተቆጣጣሪህ ማሳየት አለበት። አብዛኛው ግዜ ለማህበሩ ደረሰኝ ወይም ቅጂውን ማቅረብ አለብህ። ይህን ለማድረግ ማፈር ኡአለብህም። የበጎ ስራ በምትሰራብት ግዜ ገንዘብ ማጥፋት የለብህም!**

- **በፈለግከው ግዜ ይህን የበጎ ስራ ማቆም ትችላለህ። ለምሳሌ ስራ ካገ ህ ወይም ሌላ ማድረግ ከፈለግክ**

- **በምትሰራው የበጎ ስራ ደስተኛ ከሆንክ ለጓደኞችህ ንገራቸው!**

**Volunteer Centre Sheffield, The Circle, 33 Rockingham Lane, Sheffield S1 4FW Tel. 0114 253 6655**

This leaflet was written in conjunction with the Northern Refugee Centre, and funded by the Opportunities for Volunteering Scheme in Partnership with the Department of Health and Volunteering England

Quality accredited by | Service of | Member of National Association for Council for Voluntary Service



Volunteer Centre Sheffield is a service of Voluntary Action Sheffield.
Registered Charity No. 223007 A company limited by guarantee Registered in England & Wales No. 215695.